የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 3 እና 4

1. "የእግዚአብሔርን መንገድ አዘጋጁ። ጥርጊያውንም አስተካክሉ የሚል የአዋጅ ነጋሪ ቃል እነሆ በገዳም አለ።" ብሎ ትንቢት የተናገረው ማን ነው?
ሀ) ኤርምያስ ለ) ዳዊት ሐ) ኢሳይያስ መ) ሆሴዕ

2. ጌታ ለምን በ30 ዘመኑ ተጠመቀ?
ሀ) አዳም በ30 ዓመቱ ተፈጥሮ በ40 ቀኑ የተገኛትን ልጅነት ለመመለስ
ለ) እንደ አጋጣሚ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በዚያ ጊዜ ያጠምቅ ስለነበር
ሐ) ሄሮድስ ዮሐንስን ሳያስገድለው ቀድሞ ለመጠመቅ
መ) ሁሉም

3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው በስንት ዓመቱ ነበር?
ሀ) 15 ለ) 30 ሐ) 33 መ) አይታወቅም

4. "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህስ አንተ ራስህ ወደ ታች መር ብለህ ውረድ። በመንገድህ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክትን ስለ አንተ ያዝዛቸዋል..." ብሎ ሰይጣን ጌታችንን የፈተነው በየትኛው ኃጢአት ነው?
ሀ) ስስት ለ) ትዕቢት ሐ) ፍቅረ ንዋይ መ) ሁሉም

5. ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 40 ቀን ከጾመ እና በሰይጣን ከተፈተነ በኋላ ወዴት አቀና?
ሀ) ወደ ቤተልሔም ለ) ወደ ኢየሩሳሌም ሐ) ወደ ገሊላ መ) ሀ እና ለ

6. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ጌታ በምኩራብ ያነበበው መጽሐፍ ምን ነበር?
ሀ) መዝሙረ ዳዊት ለ) መጽሐፈ ኢሳይያስ ሐ) ከብሔረ ኦሪት አንዱ መ) መጽሐፈ ኢያሱ

7. ጌታ በናዝሬት በምኩራብ ከተጠቀመባቸው ምሳሌዎች ውስጥ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) የሰራድታዋ ሴት ለ) ሶርያዊው ንዕማን ሐ) መጥምቁ ዮሐንስ መ) መልሱ የለም

8. ጌታ ባደገበት በናዝሬት ሲያስተምር...
ሀ) የአንደበቱን ቅልጥፍና አደነቁ
ለ) በትምህርቱ ተደስተው ተከተሉት
ሐ) ገፍተው ይጥሉት ዘንድ ወደ ተራራ ጫፍ ወሰዱት
መ) ሀ እና ሐ

9. የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት የምን ጥምቀት ነበረች?
ሀ) የልጅነት ለ) የንስሐ ሐ) የክርስትና መ) ሁሉም

10. መጥምቁ ዮሐንስ ሄሮድስን የሚገሥጸው ስለምን ነበር?
ሀ) ግብረ ሰዶም ይሠራ ነበርና
ለ) ነፍስ ሳያስገድል አይውልም ነበርና
ሐ) የወንድሙን ሚስት አግብቶ ነበርና
መ) ሁሉም

11. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ላይ ጌታችን ያወጣውን ጋኔን "ዝም በል" በማለቱ ለእኛ ምን አስተማረን?
ሀ)ጋኔን እንዲያወራ እና እንዲለፈልፍ መፍቀድ እንዳለብን
ለ)የሐሰት አባት ነውና የሚያወራው ከእውነቱ ሐሰት ይበልጣልና አለመስማት
ሐ) ለጋኔን የሚናገርበት እድል አለመስጠት
መ) ለ እና ሐ

12. ዲያብሎስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በምን በምን ፈተነው?
ሀ)ዝሙት፣ ስስት፣ ትዕቢት
ለ)ትዕቢት፣ ፍቅረ ንዋይ፣ ስስት
ሐ)ዝሙት፣ ፍቅረ ንዋይ፣ ክህደት
መ)ሁሉም

13. “ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል ተብሎ ተጽፎአልና” ይህንን ጥቅስ በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እናገኘዋለን?
ሀ)መዝሙረ ዳዊት 90
ለ)ትንቢተ ኤርሚያስ ምዕራፍ 7
ሐ)ትንቢተ ሐጌ ምዕራፍ ፩
መ) መልስ አልተሰጠም

14. መጥመቁ ዮሐንስ ለቀራጮች ምን ብሎ አዘዛቸው?
ሀ)ሁለት ልብስ ያለው አንዱን ለሌለው ይስጥ
ለ)ምግብ ያለው ለሌለው ይስጥ
ሐ)በደመወዛችሁ ኑሩ
መ)ከታዘዛችሁት በላይ አትውሰዱ

15. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከከተማ አውጥተው ገፍተው ከተራራ ሊጥሉት ሲሉ ምን አደረገ?
ሀ)እንዲጥሉት ፈቀደላቸው
ለ)በመካከላቸው አልፎ ሄደ
ሐ)መላእክቱን እንዲቀስፏቸው አዘዘ
መ)ሁሉም

16.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድረ በዳ ከጾመ በኋላ
ሀ)ድንጋይን ዳቦ አደረገ
ለ)ተራበ
ሐ) በዲያብሎስ ተፈተነ
መ)ለ እና ሐ

17.የሉቃስ ወንጌል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ዘር ሐረግ ሲቆጥር _____ ብሎ ጀምሮ _____ብሎ ጨረሰ።
ሀ) የዮሴፍ ልጅ.....የአዳም ልጅ
ለ)የሜልኪ ልጅ.....የሴት ልጅ
ሐ)የዮሴፍ ልጅ.....የእግዚአብሔር ልጅ
መ)መልስ አልተሰጠም

18.መንፈስ ቅዱስ ጌታችን ሲጠመቅ በምን አምሳል ወረደ?
ሀ)በእሳት ለ)በነፋስ ሐ)በርግብ መ)ሁሉም

19.መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በሚያስተምርበት ጊዜ ሊቃነ ካህናት የነበሩት እነ ማን ናቸው?
ሀ)ሐናና ቀያፋ
ለ)ሄሮድስ እና ዮሴፍ
ሐ) ጲላጦስ እና ሔሮድስ
መ)ዘካርያስ እና ኒቆዲሞስ

20. "ነገር ግን የጫማውን ጠፍር መፍታት ከማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ ይመጣል" ብሎ መጥምቁ ዮሐንስ የመሰከረው ስለማን ነው?
ሀ)ስለቅዱስ ጴጥሮስ
ለ)ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ሐ)ስለማቴዎስ
መ)ስለቅዱስ ሉቃስ